# ዜና ገመድ ፓምፕ

I ዕትም:ቁ.1 23/9/2005

## - ንፁህ፤ዉሃ፤ጥሩ ጤንነት፤መልካም ሕይወት-

ገመድ ፓምፕን ለመጠጥ ዉሃ በማሰራጨት የገጠርን የንጹህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት፤ንፅሕና (ሳኒቴሽን) እና ኑሮን የማሻሻል ፕሮጀክት

## የእንኳን ደህና መጣችው መልዕክት ከሚኒስተራችን

ለዚህ ኒዉስ ሌተር (ዜና ገመድ ፓምፕ) የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ የዉሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ክቡር አቶ አለማየሁ ተገኑ በዚህ ፕሮጀክት ላይ ያላቸዉን ታላቅ ተስፋ ገልፀዋል፡፡በኢትዩጵያ ውስጥ የሚካሄዱ የዉኃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን ሥራዎች ህዝባችንን የሚረዱ በጣም ጠቃሚ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ናቸዉ፡፡የንፁህ መጠጥ ዉሃ አቅርቦት ለሀገራችን እድገት መፋጠን እና ለህዝቡ ጤና መሻሻል የሚጫወተዉ ሚና ትልቅ ነው፡፡ በገጠር ያሉትን አርሶ አደሮች ከመርዳቱም በላይ በኢኮኖሚ፤በማህበራዊ፤እና በፓለቲካዊዉ እንደምታ ላይ የሚያሳደረዉ ተፅዕኖ የትየለሌ ነዉ፡፡በ2007 ዓ.ም የዉሃ አቅርቦትን ሽፋን ወደ 98.5 % ለማደረስ ያቀድን ሲሆን፣ለዚሁ የቀረን ጊዜ ሁለት ዓመት ብቻ ነዉ፡፡አሁን ያለንበት የዉሃ አቅርቦት ሽፋን 61.1% ላይ ነዉ ፡፡ ይህ የሚያሳየን ብዙ መሥራት እንዳለብን ነው፡፡ላስቀመጥነዉ ግባችን ይረዳን ዘንድ ይህን በጃፓን አለም አቀፍ ትብብር ኤጀንሲ(JICA) እገዛ የሚከናወነዉን ገመድ ፓምፕን ለመጠጥ ዉሃ በማሰራጨት የገጠርን የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት፣ንፅሕና (ሳኒቴሽን) እና ኑሮን የማሻሻል ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ሙሉ እገዛ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑንም ገልፀዋል፡፡



ክቡር አቶ አለማየሁ ተገኑ
ሚኒሰተር,
ዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር

---

## ስለ ፕሮጀክቱ ምን ያህል ያዉቃሉ ?

ፕሮጀክቱ የተጀመረዉ በመጋቢት ወር በዚሁ አመት ነዉ፡፡ ሥራዉን የሚያከናዉነው በዉሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና በጃፓን አለም አቀፍ ትብብር ኤጀንሲ (JICA) በጋራ ትብብር ነዉ፡፡ ዓላማዉም ለንፁህ የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት የገመድ ፓምፕ በማሰራጨት በገጠር ዉሃ አቅርቦትን፤ንፅህናን እና ኑሮን ለማሻሻል የታለመ ነዉ ፡፡ለበለጠ መረጃ በቀኝ በኩል የተቀመጠዉን ሳጥን ይመልከቱ፡፡

> የፕሮጀክቱ ዘመን፡ መጋቢት 2005 እስከ ታህሳስ 2008
> ፈጻሚዉ አካል ፡ የመጠጥ ዉሃና ሳኒቴሽን ዳይሬክቶሬት የዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ፤የደቡብ ብሔር ፤ብሔረሰቦችና ህዝቦች (በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ)የዉሃ ሀብት ቢሮ፤
> ፕሮጀክቱ የሚከናወንበት ቦታዎች ፡ 4 ወረዳዎች /አከባቢዎች በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ

## ከፕሮጀክቱ የሚጠበቁ ዉጤቶች

1 ለመጠጥ ዉሃ የሚያገለግል የገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ ወጥነት ያለዉ ገላጭ ሰነድ ይዘጋጃል፡፡

2 ለመጠጥ ዉሃ የሚያገለግል የገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ የአመራረትና አተካከል የእስትራቴጂ ሰነድ ይዘጋጃል ፡፡

3 የገጠር ኑሮ የመጠጥ ዉሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን በታለሙት አከባቢዎች ይሻሻላል ፡፡

4 ለመጠጥ ዉሃ የገመድ ፓምፕን ለማሰራጨት መመሪያ ይዘጋጃል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃም ይተገበራል ፡፡የጃፓንና የሀገር ዉስጥ ባለሞያዎች በሰፊዉ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡

## የፕሮጀክቱ ማእቀፍ



# የፕሮጀክቱ ጅማሮ

## የመጀመርያዉ የጋራ አስተባባሪ ኮሚቴ እና የመሪ ኮሚቴ በሚያዚያ 8 እና በሚያዚያ 11 /2005 ዓ.ም ስብሰባ አካሄዱ

‘’በራስ አቅርቦት የገጠር መጠጥ ዉሃን ማዳረስ’’የሚለዉ የፕሮጀክቱ ዓላማ መሆኑን የፕቶጀክቱ ዋና አማካሪ ወ/ሪት አኪኖ አዉስቶ ይህንኑም እንዴት ቀስ በቀስ ማስረፅ ይቻላል የሚለዉን በመጀመርያዉ የጋራ አስተባባሪ ኮሚቴ እና የመሪ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ መመከሩን ገልፀዋል ።

የመጠጥ ዉሃ እና ሳኒቴሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዩሐንስ በበኩላቸዉ መንግሥት በመጠጥ ዉሃ ፣ሳኒቴሽንና ሥነ ጤና ፕሮግራም ላይ ያለውን ፖሊሲ አስረግጠዉ ሲገልፁ አቶ ሁሳሚም ይህ የገመድ ፓምፕ ፕሮጀክትም ከመንግሥት ፕሮግራም ጋር በጥምረት የሚሰራ እና ዉጤቱም መንግሥት ላስቀመጠዉ ግብ እገዛ እደሚያደርግ ገልፀዋል።



**የመጀመሪያዉ የጋራ አስተባባሪ ኮሚቴ ስብሰባ**
በግራ በኩል; ወ/ሪት አኪኖ(ፒ.አ), አቶ ኤፍሬም(ጃይካ),አቶ ሱሚ(ጃይካ), አቶ ዩሃንስ(ከዉሃና ኢነርጂ), ዶ/ር ማርቆስ(ከዉሃና ኢነርጂ), ዶ/ር ተገኑ (ከዉሃና ኢነርጂ), አቶ ግርማ(ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ)



የመጀመርያዉ የመሪ ኮሚቴ ስብሰባ

የሴክተር ሰፖርት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር ማርቆስ ሌሎች ዘርፎችን ለምሳሌ የጤና፣የግብርና፣የፋይናንስ፣የትምህርት ወዘተ ማሳተፍ በጣም አስፈላጊ መሆኑን አበክረዉ ከገለፁ ቡኃላ እያንዳንዱ አባል አስፈላጊ መረጃ ማቅረብ እዳለበት ቤቱም ተስማምቶበታል።የፕሮጀክት ብድኑም ሁለቱ ዋና ዋና ሥራዎች(የገመድ ፓምፕ ማሻሻል እና የቦታ መረጣ )በቀጣዩ ወር እንደሚጀመር ገልፀዋል ። በመጨረሻም ከዉሃና ኢነርጂ እና ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የመጡ ተሳታፊዎች በፕሮጀክቱ እቅድ ላይ ተስማምተዋል፤ ፕሮጀክቱም በይፋ ሥራዉን መጀመሩን አብስረዋል።

### መጋቢት እና ሚያዚያ የተከናወኑ ሥራዎች .

| | |
|---|---|
| መጋቢት18 | የጃፓን የኤክስፐርት ቡድን መጣ |
| መጋቢት 19 | ለዉሃና ኢነርጂ ምክትል ሚኒስተር ጥሪ ተደረገ |
| ሚያዚያ 8 | የመጀመርያ የጋራ አስተባባሪ ኮሚቴ ስብሰባ ተደረገ |
| ሚያዚያ 11 | የመጀመርያ የመሪ ኮሚቴ ስብሰባ ተደረገ |

### በግንቦት እና በሰኔ የታቀዱ ሥራዎች.

- የገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች አሰሳ ጥናት
- የሙከራ ጉድጓድ ቁፋሮ (ለጉድጓድ ማሻሸያ)
- በግብርና፤ማይክሮ ፋይናንስ እና በሐይጂን ላይ መረጃ መሰብሰብ
- ፕሮጀክት ወረዳዎች/አከባቢዎች በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ መረጣ ማካሄድ
- ገመድ ፓምፕ ማሻሻል



የገመድ ፓምፕ ላይ ገለፃ ሲደረግ



የገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች አሰሳ ጥናት በከፊል

*ማንኛዉንም አስተያየት ፣ጥያቄዎች ሐሳብ ካላችሁ በዚህ አድራሻ ተጠቀሙ*

ጃይካ ሮፕ ፓምፕ ፕሮጀክት
ክፍል # 016, በዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር
ስልክ: +251 - (0)11-651-1455
ሞባይል: +251 - (0)935-353210/11

Webiste
【MoWE】http://www.mowr.gov.et/
【JICA】http://www.jica.go.jp/ethiopia/english/office/index.html
E-mail jica.ropepump.ethiopia@gmail.com